## ፖለቲካና እግር ኳስ በሎስአንጀለስ
## ያመኑት ፈረስ ጣለ በደንደስ

ኢፍትን

**ዝክረ ነገር (ከአሜሪካ)**

ለ23ኛ ጊዜ የሚካሄደውን በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያውያን እግር ኳስ ፌዴሬሽን ለመጎብኘት በሎስአንጀለስ ከተማ ድፍን ሰባት ቀን ቆየሁ:: ነበልባላማ አዘል ከሆነው የዋሽንግተን ዲሲ እምክ አየር የሎስአንጀለሱ ሞቃታማ ቢሆንም እጅግ የተሻለ ነበር::

እንሆ ኳስ ተከትዬ፣በኳስ ሰበብ ዘመድ አዝማድ ፣የድሮ አብሮ አደግ ጓደኛ ለመጠየቅና፣ ስደት የሸነቆረውን የመንፈስ ቀዳዳ ለጊዜውም ቢሆን ለመድፈን በእየአመቱ የፈረንጅ ሀምሌ ግም ባለቁጥር ከከተማ ከተማ ስዘዋወር ሀያ አንድ አመት አለፈኝ:: በእግር ኳስ ወቅት እኛ አዛውንቶች ሌላ ተግባር የለንም በእግር ኳስ ስም ተሰብስቦ ወግ መጠረቅ፣የነበርንበትንም ሆነ ጭራሽ ያልሰማነውን የፖለቲካ ሁኔታ በግረድፍ መሰለቅ፣ማማትና መተማማት ትልቁ ሥራችን ነው:: "ድመት መንኩሳ አመሏን አትረሳ" እንዲሉም የዕድሜ መለያችን የሆነ ግራጫ ጠጉራችን ወደ ጥጥነት ቢቀየርም የፖለቲካ ሀሜት ካልሰለቅንና ዕድሜ የማይለውጣቸውን ነባር ወይዛዝርት የጎሪጥ ካላየን ኳሱም ጉዞውም የተሟላ አይመስለንም::

መኖር ድንቅ ነው፣ዕድሜንም ህይወትንም ያሳያል የዛሬ ሀያ አንድ አመት በአንቀልባ ታዝለው ኳስ ሜዳ የመጡ ህፃናት ዘንድሮ ሸበል ኮበል ሆነው ወንዶች በጆሯቸው ላይ ጉትቻ፣ሴቶች ደግሞ በማህል እንብርታቸው ላይ ሰነሰለት አስረው መጥተዋል:: ጀግኖቹ ወጣቶች በምንተዳዬ( who cares) አተያይ፣የእኔ ቢጤውን ሸማግሌና ነባር ፖለቲከኛውን የባህል ልዩነት በሚሉት ምህታት ሲያሸማቁት ነበር የሰነበቱት::

ድሮ አዲስአበባ ስታዲዮም ግራ ጥላ ፎቅ ተቀምጠን እኛ የኮረፌ ተራንና የካታንጋን ሰዎች የጎሪጥ እያየን፣በቀኛችን በኩል ደግሞ በመልካም የአጎበር መቀመጫ ጉብ የሚሉት ባለጠጎች ፣መኳንንትና ሹማምንቶች እኛን በሸውራራ አይን እያዩ " ኳስ ሜዳና የእንጠጦ ጎርፍ የማይሰበስበው የለም" ይሉን እንደነበረው የሎሰአንጀለስ የኮሎሲየም ስታዲየም ከዘመናዊ ደብተራ እስከ ቃልቻ፣ከአውቆ አበድ እስከ ጭምት፣ከሀሳዊ ዕሀፍት እስከ መፅሀፍ አዟሪ፣ከውሸት ምሁራን እስከ ጠበብት፣ከአዝማሪ ፖለቲከኛ እስከ አቋጥሩኝ ባህታዊ፣ከወይዛዝርት ደላላ እስከ ቁጭ በሉ ጋዜጠኛ፣ከነገር

ከታቢ እስከ ጠበቃ ፣ከዘመናዊ ጌታ እስከ ስልጡን አሽከር፣ከፋንጋ እስከ ቆንጆ፣ከተላላ ወጣት እስከ አዛውንት ፖለቲከኛ ሁሉንም እንደአመሉ አስተናግዷል፡፡

በዘንድሮው የሎስአንጀለስ እግር ኳስ ጨዋታና በዓል ላይ አዘጋጂዎቹ ከ 50 ሺህ በላይ ሰው ይመጣል ብለው ቃላቸውን ቢሰጡም የተገኘው ሰው ቁጥር ከ8 ሺህ አይበልጥም፡፡ ዘጠና አራት ሺህ ሰው በሚይዘው ግዙፍ ስታዲየም ውስጥ "ዶሮ በጋን" እንዲሉ በግራ ትሪቡን በኩል በጥቂቱ ተበታትነን ነበር የምንቀመጠው፡፡ በፌዴሬሽኑ ውስጥ ከሚሰሩ የጥንት ወዳጆቼ እንደሰማሁት ብዙ ሰው መጥቷል በተባለበት ማለትም አርብ ጁላይ 7 ቀን የተገኘው ገቢ 92,000 ዶላር ሲሆን የመግቢያ ዋጋውም በነፍስ ወከፍ 12 ዶላር ነበር፡፡ ስለዚህ የሎስአንጀለስ ኮሎሲየም እንደካንቦሎጆ ማሾለኪያ ቀዳዳ ከሌለው በስተቀር በሂሣቡ ስለት መሠረት ተስተናጋጅና አስተናጋጅ ቁጥሩ ከ 8 ሺህ አይዘልም፡፡

ሀያ ሦስተኛው የእግር ኳስ ፌሽታ ከመቼውም ጊዜ በሚያስገርም ሁኔታ ልዩ የሆነ ለውጥ የታየበትን ያህል ያው እንደቀድሞው ሁሉ በጭራሽ ያልተለወጡ ነገሮች ገዝፈው የታዩበት ነበር ለማለት ይቻላል፡፡

ሀ. በመጀመሪያ ከአመት ወደ አመት በማይለውጡት ወይም ፌዴሬሽኑ ሊለውጣቸው በማይፈልጋቸው ወይም በማያስባቸው ጉዳዮች ላይ ላተኩር፡-

- ያልተለወጡ ከሚባሉ ጉዳዮች መካከል አንደኛው የእግር ኳስ ፌዴሬሽኑ ከዚህ በፊት ታይቶና ተስምቶ በማይታወቅ ሁኔታ በስታዲዮሙ የድምፅ ማጉያ እየታገዘ ከማንም ያልወገንኩ፣ከፖለቲካና ከሀይማኖት ተፅዕኖ ነፃ የሆንኩ ድርጅት ነኝ በማለት በቃለመሀላ ቢገልፅም፣ዘንድሮም እንደአለፉት አመታት ሁሉ ከፖለቲካ ወገንተኝነቱና በተለይም ከአንዳንድ የፖለቲካ ነውጠኞች ተፅዕኖ ነፃ መሆኑን በሚያሳምን መልኩ ማቅረብ አልቻለም፡፡ አገር ባወቃቸውና በሞቃቸው አዛውንትና አሮጊት ነውጠኞች በኩል ነጎድጓዳማ  በሆነው የድምፅ ማጉያ ነፃ ነኝ ቢልም የሚያምን አልነበረም፡፡ በተለይ የኢትዮጵያ ቀን ተብሎ በተነገረለት ፌስቲቫል ላይ ፕሮግራሙን ይመሩ የነበሩትን መበልትና በቦታ ርቀት ምክንያት የክስ ቻርጃቸው ቀረላቸው የተባሉት የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያ ጋዜጠኞች የፖለቲካ ሰርጎገብ ወይስ ፖለቲካ የያሙ የማርያም ባህታዊያን? እያለ ሰው ተሳልቆባቸዋል፡፡

- ሌላው የማይቀየር ነገር ጉዳይ ደግሞ በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ የእግር ኳስ ፌዴሬሽን ኢትዮጵያ የሚለውን የወል ስም በመጠሪያነት የሚጠቀም ቢሆንም

ውብና ዕንቁ የሆኑ የአገራችን ብሄሮች፣ጎሣዎችና ሕዝቦች ቢያንስ ለምልክት እንኳን ያህል ያልተወከሉበት ሆኖ ቀጥሏል። አሁንማ ይባስ ብሎ ከክፍለ ሀገር ወርዶ ወደ አንድ ከተማ ከከተማም የአንድ ሰፈር የቀድሞ ልጆች ማህበር መስሎ አርፏታል።

- የእግር ኳስ ፌዴሬሽኑ ነባርና ከቶ የማይቀየር ሌላ ባህሪ ደግሞ የንዋይ ፍቅር ነው። በባንክ ያለና ወደ አንድ ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ እያገላበጠ አሁንም ካናቴራ፣ቅርፃ ቅርፅ፣ፖስተር፣ስዕል፣መፅሀፍ፣ሲዲ፣ለሚሸጡትና ምግብ ለሚያበስሉ ወገኖች የድንኳን ኪራይ በነፍስ ወከፍ 3 ሺህ ዶላር አይኑን በአሞሌ ጨው አጥቦ መሸጥ መቀጠሉ ነው። የክፍያው ቀላድ በተሰፈኛ ነጋዴዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በምግባር ሰናይ ተግባር ላይ ተሰማርተናል በሚሉና የሀይማኖት ተቋማት ናቸው በሚባሉ ድርጅቶችም ላይ መጣሉ ያስገርማል።

- ፌዴሬሽኑ እንደ ሞጃ ሰዎች የቅንጦት ወጪው በርከትከት ቢልም ከወጪ ቀሪውን በሁነኛ ኦዲተር አሠርቶ ኦፊሴላዊ ያለማድረጉ አሁንም የቀጠለ አባዜ ነው። ለሁሉም ይችን ሰሞን ለፖለቲካ ሎቢስቶች የምንከፍለው ገንዘብ አጠረን፣እጃችንም ደረቀ የሚሉ አይን አውጣ የስደተኛ ፖለቲከኞች ስለተበራከቱ ተመልካች አለና ካዝናውን አጥብቆ መዝጋት ተገቢ ሳይሆን አይቀርም።

ለ. በወሳኝ ሁኔታ ወደተለወጡ ሁኔታዎች ስንመለስ የዘንድሮው በዓል ጉልህ፣ የሚታዩና የሚዳሰሱ ሁለት ለውጦች አሳይቷል።

- አንደኛውና ትልቁ ለውጥ ዘንድሮ ሎስአንጀለስ የስደት ፖለቲከኞችን አሳፍሯል፣አሸማቋል። ለስፖርትና ለባህላዊ ትስስር የተሰባሰበው ኢትዮጵያዊ ፖለቲከኞችን ያለአንዳች ማመንታት በዝራር አሽንፏል።

  ያልተጠራ ስብሰባ፣ያልተነፋ የሰልፍ ጥሩንባና እምቢልታ፣አልነበረም። እንደ በዓሉ ዋዜማ ከሆነ የስፖርት ሳይሆን የፖለቲካ ፌስቲቫል በሚመስል መልኩ ሽር ጉዱ ጦፎ ነበር። ስብሰባ ቀንና አዳራሽ ሽሚያም የሚያስደንቅና የሚያስገርም ነበር። ያልተረጨ የፖለቲካ ወረቀት፣ ያልተበተነ ማስታወቂያ፣ያልተለጠፈ ፖስተር አልነበረም። አንዳንዱ ምግብና መጠጥ ቤትማ መግቢያና መውጫው በፖስተሮች ብዛት ከንግድ ቤት ወደ ማስታወቂያ ስሌዳነት ተቀይሮ ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም።

የፖለቲካ ስብሰባውን በፖርቱጋል ቋንቋ አሀዱ ብለው የከፈቱት የአውሮፓ ፓርላማ መበልት የሆኑት እመት " አና ጎሜዝ " ሲሆኑ እርሳቸውም ወደ ሎስአንጀለስ የከነፉት "Ethiopian American Council" እየተባለ በሚጠራውና የአንድ ግለሰብ የግል ኩባንያ በሆነ ድርጅት ተጋብዘው ሲሆን ንግግራቸው ሳይጥም፣ የማንንም ቀልብ ሳይስቡ፣ጉንጭ አልፋ ጉራማይ ንግግር አድርገው በመጡበት ተመልሰዋል:: በዚህ ስብሰባ ላይ ወደ 80 ያህል አዛውንት ፖለቲከኞች የተሳተፉ ቢሆንም እንደተለመደው ሊሰሙት በሚፈልጉት ረክተው፣የማይፈልጉትን ደግሞ አጣጥለው ሄደዋል:: ስብሰባው የተካሄደው ባረፍኩበት ሆቴል ውስጥ በመሆኑ በስብሰባው አብረውን የተቀመጡ አንድ አዛውንት ያሉኝ ነገረ ቢኖር " በሴትየዋ ንግግር እረክቻለሁ ይሁን እንጂ አባቶቻችን ያላደረጉትን የነጭ አምላኪነት ባህሪ ደግሞ ጠልቻለሁ" ብለውኛል::

አና ጎሜዝ ያደረጉት ፕሮፖጋንዳ አዘል ንግግር ጋብ ሳይል ለጥቀው የቀረቡት የአሜሪካው ኮንግረስ አባል Christopher Smith ስታፈር ሚ/ር ግሬግ አለቃቸው በኢትዮጵያ ላይ ያቀረቡት "የግንፍልፍልና የመሸታ ቤት" ረቂቅ ህግ እንዲያልፍ እንደሚጥሩ ነገር ግን "የኢትዮጵያና የአሜሪካ" ግንኙነት ጥልቀት ያለውና ጠንካራ በመሆኑ ይህ ሕግ እንዲያልፍ የምትፈልጉ ሰዎች ተጠንቀቃችሁ ተጓዙ ማለታቸው "የሳንሆዜን ወጠጤ " ፖለቲከኞች ስሜት ነክቷል:: በዚህ ስብሰባ ላይ መጋቢና አሳላፊ ሆነው የቀረቡት በፈረንጅኛ አፍ "አል ማሪያም" ብላችሁ ጥሩኝ የሚሉት አለማየሁ ገብረማርያም ከመካከላችን ከአዲስ አበባ ተነስታችሁ እኛን ልትሰልሉ የመጣችሁ ካላችሁ ለአለቆቻችሁ እኛ የሰላም ሰዎች መሆናችንን ንገሩልን ብለው መግለፃቸው በስብሰባው ላይ የታደመውን ተስፈኛ ፖለቲከኛና ቱሪናፍ እርስ በእርሱ የጎሪጥ እንዲተያይ አድርጎታል::

- ብዙ የተነገረለትና አዳራሽ የማይችለው ስብሰባ ይሆናል ተብሎ የተለፈለፈለት የቅንጅት፣የኦነግና የኦጋዴን ነፃ አውጭ ድርጅቶች "የለበጣ ጥምረት" ስብሰባ እንዳረጋቸው ፅጌ፣ብርሀነ መዋ፣አባ ቢያና፣ስማቸውን ለጊዜው የማላስታውሰው የኦጋዴን ተወካይና ከሻላቅነተ ወደ አርበኝነት ተቀይረናል የሚሉ በሱፍና በክራባ የተንቆጠቆጡ ሁለት ወረቀት አርበኞች ቢገኙም ስብሰባው ገዥውን ፓርቲ ከማወገዝ ያለፈ ተግባር አልነበረውም:: ያለማጋነን በዚህ ካልቨር ሲቲ በምትባል ትንሽ ከተማ በተካሄደ ስብሰባ 120 ያህል የቅንጅትና የኦነግ ደጋፊና አባላት ተገኝተዋል:: አቶ አንዳርጋቸው ኢህአደግ ባስተማሯቸው አፍ እየታገዙ ከ50 ጊዜ በላይ ወያኔ/ኢህአደግ

ማለታቸው ጠርጥር ከገንፎ መሀል አለ ስንጥር የሚያሰኝ ሳይሆን አይቀርም፡፡

- ሌላው ደግሞ በሎስአንጀለሷ የቅድስት ማርያም የተካሄዱት ስብሰባዎች ማርያም ተቆጥታ ይሁን ወይም ሰው ተግባራቸውን በመጠየፍ እንደሆነ ባላውቅም፣ኢሕአፓ በጠራው ስብሰባ ላይ የተገኙት ሰዎች ቁጥር 32 ብቻ ነበር፡፡ በማግሥቱ ማለትም ጁላይ 7 በአርበኞች አንድነት ግንባር የተጠራው ስብሰባ ላይ ሰው ባለመገኘቱ ሳይካሃድ ቀርቷል፡፡

በሌላም በኩል የሎስአንጀለስ ከተማን ሊያንቀጠቅጥ ነው ተብሎ የተነገረለተ ቅንጅት ሰላማዊ ሰልፍ የዕቃ ዕቃ ጨዋታ ሆኖ ነው የቀረው፡፡ በሰልፍ ላይ የተገኑት 14 ሰዎችና በወረቀትና በፖስተር የተለበዱ 3 መኪናዎች ብቻ ነበሩ፡፡ በሰልፍ ላይ ከቅንጅቱ አመራሮች መካከል አንዳንዶቹ ቢገኙም ሌሎች የፀሐይ ጨረር በመፍራት ይመስላል "ፓል ቶክ" በተባለው የኢንተርኔት መወያያ መድረክ ውስጥ መቆየትን መርጠዋል፡፡

ፖለቲከኞች ዘንድሮ አልቀናቸውም አደንቋሪ ጩኸታቸውን ሰው መስማት አልፈለገም የእነሱ ልብና ኳስ ሊመለከተው የመጣው ኢትዮጵያዊ ፍላጎት የእየ ቅል ሆነዋል፡፡ በውጭ አገር የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ፖለቲከኞች ወይም የእነርሱ ደጋፊዎች ነን ብለው የሚያምኑ ከሆነም በጭራሽ ተሳስተዋል፡፡ በአጭሩ ኢትዮጵያዊው የኳስ ሜዳ ፖለቲካን እምብየው እንዳለ በግልፅ ታይቷል፡፡ የሚያስገርመው ግን ይህ ገሀድ ኩነት ፖለቲካ አነሠን ለሚሉት ለቪኦኤ ጋዜጠኞችና ለአዝማሪ ፖለቲከኞች ግልፅ ያለመሆኑ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ቀን ተብሎ አርብ ዕለት በተከበረው በዓል ላይ ሁሉም ተጋባዥ እንግዶች ጨዋ በሆነ ቋንቋና ከፖለቲካ በፀዳ አንደበት ስለኢትዮጵያ ባህል፣ታሪክ፣ህዝብና እንግዳ ተቀባይነት አድናቆታቸውን ገልጸዋል፡፤ የክብር አንግዳው አዛውንቱ ክቡር ፕሮፌሰር ፓንክረስት ስለፍቅር ስላምና ትብብር ሰብከዋል፡፡

ይሁን እንጂ ያላዋቂ ሳሚ "ምንትስ" ይቀባል፡፡ እንደሚባለው በእየደረሱበት እንደአልቢን ጥይት ይባርቃሉ የሚባሉት የኮንግረስ አባል Maxine Waters ወይም በጥቁር አሜሪካውያኖች Mad Max እየተባሉ የሚጠሩት ወፈፌ በማያገባቸው ገብተው ስለ " ethnic Politics" ዘባርቀዋል፡ በአሜሪካ ኮንግስ ውስጥ እጅግ ተስፈንጣሪ ናቸው የሚባሉት እኒህ ሰው ብዙ ሰዎችን አስቆጥተዋል፡፡

ለምንስ በዚህ ተግባር ውስጥ ገብተው ይዘባርቃሉ ሲሉ ብዙዎች ኢትዮጵያዊያን በአካል ሄደው አነጋግረዋቸዋል።

- ሌላውና ልዩ ለውጥ የሚባለው ወጣቱ በአዛውንቱ ፖለቲከኛ ላይ ማመፅ ነው። ወጣቱ የራሱን አለም ፈጥሯል። የራሱ ሙዚቃ፣የራሱ taste አለው። ስለእግር ኳስ ደንታ የለውም፣ትልቁ ትኩረቱ በአራዳ ቋንቋ "connection" መፍጠር ነው። ወይም cool መሆን ነው።

ወጣቱ ሞቅ ያለ የሙዚቃ ጨዋታ የራፐን ድለቃ የማድመጡን ያህል ባንፃሩ የፖለቲካ መፈክር የለጠፉ ድንኳኖችን ዞር ብሎ አያያቸውም።

በተለይ ልብ ወለድ የሚመስሉ "ህዝባችንን ልቀቅ" ፣ "በኢትዮጵያ እንዳይሸጥ የተከለከለ ሲዲ፣" "ግንቦት 7" የሚሉ መፅሀፎችና ሲዲዎች ማየት ይጠየፋል። መልዕክታቸውንም ለመረዳት ግዜውን ማጥፋት አይፈልግም።

በመሆኑም ፖለቲካ መሰል መደብሮች ክፉኛ እንደከሰሩ ተከራዮች ሳይደብቁ ለአለፊ አግዳሚዎች ይናገሩ ነበር። ገዢ ያጡ የፖለቲካ መፅሐፍትና ሲዲ ዋጋቸው 20 ዶላር የነበረው ወደ 5 ዶላር እንኳን ወርዶ የሚገዛቸው አልነበረም። በሎስአንጀለስ ከተገኘው 8 ሺህ የሚደርስ ታዳሚ መካከል ያለማጋነን ከ5 ሺህ በላይ የሚሆነው ወጣትና ከ25 አመት በታች ነው ። ከወንዶች ቁጥር ይልቅ የሴቶች ቁጥር ጎልቶ ይታያል።

ለወደፊቱ ስፖርት ፌዴሬሽኑ ይህንን ማህበራዊና ያታዊ ስብጥር ግምት ውስጥ ማስገባት የሚገባው ይመስለናል። ለመሆኑ በፌዴሬሽኑ አመራር ሴቶች አሉበት? አይመስለኝም።

በአጠቃላይ የዘንድሮ የስፖርት ቀን ነባርና አዳዲስ ፖለቲከኞች በወሳኝነት በህዝብ የተሸነፍንበት መድረክ ነበር ለማለት ይቻላል። ኪሳራውንም እያንዳንዱ ድርጅት የሚያሰላው ቢሆንም እስከ ወዲኛው ያደርሰናል ብለው ያመኑትና ሊጋልቡት የቋመጡት ኢትዮጵያዊ ወጣት እንዳይነሱ እንዳይቆሙ በራፕ ዘፈን እየሰገረ በደንደሳቸው ገልብጦ ጥሏቸዋል።

ቸር እንሁን